# እውነትም እኛ ልዩ ነን

እውነትም እኛ ልዩ ነን

-በአበራ ለማ

ላለመስማማት ተዋደን
ላለመዋደድ ተስማምተን
ላለመኗኗር ተቧድነን
ላለመፋቀር ተቃቅፈን
ላለመጋባት ተጨጭተን
ይሄው ዙረን ዙረን... እዚያው ነን!
አጀብ ዘመናችንን ቸብችበን
በኪሳራችን ቶጅረን
የመጠላለፍ ጽዋችንን፤
ተራ በተራ.... ጨልጠን
ይሄው... ሃቻምናምና... ተነበርንበት
እዚያው ዞረን ዞረን... ግጥም አልንበት፤

እንግዲህ ማን አለ እንደኛ
ዞሮ ዞሮ ተነበረበት የተኛ
ማተብ ጠባቂ ሀቀኛ
ብርቅም አይደለን እኛ?...
እንደዋሊያ እንደኒያላ
እንደጭላዳ እንደሳላ
በሌላው ዓለም የሌለን
እኛኑ ታግለን የጣልን
ቀይ ቀበሮን ተመስለን
ልዩነታችንን ያሳየን...

እውነትም እኛ ልዩ ነን
ማንም ማንም ያልበለጠን
ሃቻምናምና... ተነበርንበት
ፈጥነን ሮጠን በመገኘት
ወደር አቻ ያልተቸረን
እውነትም እኛ አንደኞች ነን።
እውነትም እኛ ልዩ ነን።

ይሄው ዙረን ዙረን... ተገጣጠምን
አንድ ሳንሆን ተማምለን
ላያ ጅቦ ተመቻችተን
ጉሮሮ ለጉሮሮ ተያይዘን
እልካችንን ውጠን...
ማን አባቱ ሊደፍረን ብለን...
አንድ ራሳችንን አሸንፈን
አንድ ራሳችንን ጥለን
አንድ ራሳችንን ገለን
ባሸናፊነት እንስቃለን
“እኛ ልዩ ነን...” እንላለን።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በሽንፈታችን እንስቃለን።
በኪሳራችን እንከብራለን።
በምጸታችን እንደምቃለን።
አዎን... ልዩ ነን እንላለን።

አጀብ ጊዜያችንን ፈጅተን
ወገናችንን ነውረን
እራሳችንን አጸጽሰን
ሌላ ሌላውን ኮንነን
ይሄው ዞረን ዞረን.... እዚያው ነን፤
የእዝን ንፍሮ እየቃምን
ሰውር ሠርግ እየበላን
ለብቻችን እየሞትን
ለብቻችን እየሳቅን
ይሄው እኛነታችንን አልረሳንም
ሃቻምናምና... ተነበርነበት ዞር አላልንም
አንደኝነታችንን አለቀቅንም፤

ይሄው...
ላለመስማማት ተዋደን
ላለመዋደድ ተስማምተን
ላለመኗኗር ተቧድነን
ላለመፋቀር ተቃቅፈን
ላለመጋባት ተጨጭተን
ይሄው ዙረን ዙረን... እዚያው ነን
ሃቻምናምና... ተነበርንበት
ፈጥነን ሩጠን... ግጥም አልንበት፤
እውነትም እኛ ልዩ ነን
እውነትም እኛ ጀግኖች ነን
ወደር አቻ ያልተቸረን
አቻዮ ዲፌሮ የተሰኘን
ማንም ምንም ያልበገረን፤

እውነትም እኛ ልዩ ነን...
አንዱ ሌላውን ሲበላ እያየን
የምንስቅ የምንፈግግ ጉዶች ነን
ይሉኝታ ላይ ተኝተን
እንደር ብለን የተሸጥን
ልዩ ልዩ ፍጡር ነን
ዋልያ ነን የምንል
ጭላዳ ሆንን የምንል
ቀይ ቀብሮን የምንመስል
እውነትም እኛ ልዩ ነን
ማንም ምንም ያልታከለን
አጀብኛ የታደለን...

(ዳግም አርትኦት፣ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም.)

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com